# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና

# ትንበያ መጽሔት

## ከፌብርዋሪ 1-10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከፌብርዋሪ 11-20 እና ከፌብርዋሪ 21-28/2025

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ፌብርዋሪ 2025

አዲስ አበባ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ


እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ....- 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ....- 1 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 2 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ....- 2 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....- 2 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....- 3 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 3 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 4 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ....- 4 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 5 -

ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 11-20, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ....- 5 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ....- 5 -

ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 21-28, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 6 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 6 -

እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 7 -





ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፈው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን፣ በአንጻሩ በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ የደመና መጨመር ከመታየቱም በላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በቁሉምሳ 24.5፣ በወራቤ 8.8፣ በጅማ 7.9፣ በኢጃጂ 7.8፣ በዲላ 5.8፣ በጭራ 5.3፣ በአዋሳ 4.5፣ በእምድብር 3.1፣ በጋቲራ 2.1፣ በአማን 1.3፣ እንዲሁም በቴፒ 1.2 ሚሜ የሚደርስ ከ1-2 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 2 እና 3)፡፡ እንዲሁም አብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍል በደረቃማው የአየር ሁኔታ ስር ቆይተዋል፡፡ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከጥቂት የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ቦታዎች በስተቀር ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ካርታ 4) ፡፡


በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ ጋምቤላና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ35.0-42.0 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ካርታ 1) ።





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው
የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025
ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025
ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረዉ
የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው የፌብሪዋሪ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ አመዝኖ እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሜቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ነገር ግን በመጨረሻዎቹ ቀናቶች በጥቂት የደቡብ፣ የመካከለኛው እና የምራብ ኪስ ቦታዎች ላይ መጠነኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን ይህም የተገኘው መጠነኛ እርጥበት የአፈር ውስጥ እርጥበትን በጥቂቱ ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 5)፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፈነው የፌብርዋሪ አስር ቀናት ከጥቂት የላይኛው ስምጥ ሸለቆ ኪስ ንዑስ ተፋሰሶች በስተቀር በአብዛኛው የሀገራችን ተፋሰሶች ላይ ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ስር እንደነበሩ የተተነተኑ የውኃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 6) ፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2025

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ የፌብሪዋሪ ሁለተኛው አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት እና የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የሚጠናከሩበት ጊዜ ነው። ስለሆነም የደቡብ ምዕራብ፣ የመካከለኛው፣ የሰሜን ምሥራቅና የምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ዝናብ ማግኘት ይጀምራሉ።


በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር መንስኤ የሚሆኑት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሰሜን ምስራቅ፤ በምስራቅ፣ በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ ገፅታ ይኖራቸዋል (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖረው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ቄልም ወለጋ፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ የደቡብ እና የመካከለኛዉ ጎንደር ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ፣




ስልክ+2511155383946ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ዋግ ህምራ፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የምስራቅ እና የደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ባስኬቶ፣ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ፣ ጉራጌ እና ምስራቅ ጉራጌ፣ የቀበና፣ የጠምባሮ እና የማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ እንዲሁም የየም ልዩ ዞን እንዲሁም የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በሌላ በኩል በጋምቤላ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በደቡብ ምስራቅ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 32 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 8)።




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 11-20, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ


በመደበኛ ሁኔታ በፌብርዋሪ ሦስተኛው ዘጠኝ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ መደበኛ ቦታዎቻቸውን የሚይዙበትና የሚጠናከሩበት ጊዜ በመሆኑ በተለይም በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋንና የዝናብ ስርጭት ይኖራቸዋል፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በመጪዎቹ ስምንት ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአንጻራዊ ሁኔታ እንደሚጠናከሩ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 9)፡፡

Total Rainfall (mm) for 21-28 Feb 2025




ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 21-28, 2025

የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በሰሜን ምስራቅ፣ በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ከበልግ ወቅት መጀመር ጋር ተያይዞ በዚህ ወቅት የሚገኘው እርጥበት የበልግ አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ስለሚያሻሽል የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የበልግ ወቅት ሰብሎችን አስቀድሞ ለመዝራት የሚያስችል በመሆኑ አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት ከማሳ ዝግጅት ጀምሮ ዘር ለመዝራት የቅድመ ዝግጅት ስራ ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የፌብርዋሪ አስር ቀናት ከጥቂት የላይኛው የባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ አባይ እና የአዋሽ ኪስ ንዑስ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል አብዛኛዎቹ የሀገራችን ተፋሰሶች ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ስር እንደሚቆዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የእርጥበት እጥረት ባለባቸውና መጠነኛ እርጥበት በሚጠበቅባቸው አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለማሰባሰብ እና ለማከማቸት የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et